መልእክት አራት

## የእግዚአብሔር ቃሎች—መለኮታዊው አቅርቦት እንደ ምግብ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ ኤር. 15፡16፤ ዘዳ. 8፡3፤ ማቴ. 4፡4፤ ዮሐ. 5፡39-40፤ 6፡50-51፣ 57፣ 63፤ ቆላ. 3፡16

1. **"ቃልህ ተገኝቶአል እኔም በልቼዋለሁ"—ኤር. 15፡16፦**
   ሀ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመጀመሪያ እግዚአብሔር አለን ቀጥሎም የእግዚአብሔር ንግግር፣ ከአፉ የሚወጣው ቃል አለን—ዘፍ. 1፡1፣ 3፤ ማቴ. 4፡4።
   ለ. ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ በእግዚአብሔር-የተተነፈሱ ናቸው፤ ስለዚህ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ያሉ ቃሎች ሁሉ ከእግዚአብሔር አፍ የወጡ ቃሎች ናቸው—2 ጢሞ. 3፡16።
   ሐ. መጽሐፍ ቅዱስ እንደ የእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔር፣ የክርስቶስ፣ የመንፈስ እና የሕይወት አካል መልበስ ነው—ዮሐ. 1፡1፣ 4፤ 6፡63፤ 14፡6፣ 17፣ 20፤ 15፡7፤ 1 ዮሐ. 1፡1፤ ሮሜ 8፡2።
   መ. መጽሐፍ ቅዱስ እንደ የእግዚአብሔር ቃል ከሦስት ንጥረ-ነገሮች የተዋቀረ ነው—ክርስቶስ፣ የክርስቶስ ሞት፣ እና የክርስቶስ ትንሣኤ—ፊልጵ. 1፡20-21፤ 2፡16፤ 3፡10-11፤ 4፡13።
   ሠ. በጌታ ኢየሱስ የተነገሩት ቃሎች መንፈስ እና ሕይወት ናቸው—ዮሐ. 6፡63፦
      1. ጌታ የተናገራቸው ቃሎች የሕይወት መንፈስ አካል መልበስ ናቸው—ሮሜ 8፡2።
      2. ክርስቶስ አሁን በትንሣኤ ያለ ሕይወት-የሚሰጥ መንፈስ ነው፣ መንፈስ በእርሱ ቃሎች ውስጥ አካል ለብሷል—1 ቆሮ. 15፡45፤ 2 ቆሮ. 3፡17፤ ዮሐ. 1፡1፣ 4፤ 6፡63።
      3. መንፈሳችንን በማንቀሳቀስ ቃሎቹን ስንቀበል፣ ሕይወት የሆነውን መንፈስ እናገኛለን—5፡39-40።
   ረ. የእግዚአብሔር ቃል እንደ ምግብ እኛን ለመመገብ የሆነ መለኮታዊ አቅርቦት ነው—ዘዳ. 8፡3፤ ማቴ. 4፡4፦
      1. የእግዚአብሔርን ቃል በተመለከተ መለኮታዊው ጽንሰ-ሃሳብ የምንመገብበት ምግብ መሆኑ ነው—1 ቆሮ. 3፡1-2፤ ዕብ. 5፡12-14።
      2. የእግዚአብሔር ቃል እግዚአብሔር ራሱ እንደ ምግባችን ነው—ዮሐ. 1፡1፣ 4፣ 14፤ 6፡33፣ 51፣ 57።
      3. ጌታ ኢየሱስ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን ቃል እንደ እንጀራው ወሰደ በእርሱም ኖረ—ማቴ. 4፡4።
      4. ከእግዚአብሔር አፍ የሚወጣ ቃል ሁሉ እኛን የሚመገብ መንፈሳዊ ምግብ ነው፤ ልንኖርበት የሚገባው ምግብ ይህ ነው—ዮሐ. 6፡51፣ 57።
      5. በእርሱ ንጥረ-ነገር እንቀናበር ዘንድ እንደ ምግባችን በቃሉ በኩል እግዚአብሔር ብልጥግናዎቹን ወደ ውስጡ ማንነታችን ውስጥ ያድላል።
   ሰ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባለው መላው መገለጥ መሠረት የእግዚአብሔር ቃሎች እንበላቸው ዘንድ ለእኛ መልካም ናቸው፣ ልንበላቸውም ያስፈልገናል—መዝ. 119፡103፤ ማቴ. 4፡4፤ ዕብ. 5፡12-14፤ 1 ጴጥ. 2፡2-3፦
      1. እግዚአብሔር ሰው እንዲበላው፣ እንዲፈጨው እና እንዲያዋሕደው ይሻል—ዮሐ. 6፡50-51፣ 57።
         ሀ. መብላት ከእኛ ውጪ ያሉ ነገሮችን መንካት እና ወደ ውስጣችን መቀበል ነው፣ በውጤቱም በመጨረሻ ቅንብራችን ይሆኑ ዘንድ ነው—ዘፍ. 2፡16-17።
         ለ. መብላት ምግብን ወደ ውስጣችን መውሰድ ነው ይህም ሕይወታዊ በሆነ መንገድ ወደ ውስጣችን ይገባና ይዋሐድ ዘንድ ነው—ዮሐ. 6፡48፣ 50።
         ሐ. በእኛ እንደ ምግብ የተበሉት፣ የተፈጩት እና ከእኛ ጋር የተዋሐዱት የእግዚአብሔር ቃሎች በእውነቱ እኛን ይሆናሉ፤ ይህ ቃሉ ቅንብራችን መሆኑ ነው—ማቴ. 4፡4፤ ቆላ. 3፡16።
      2. መጽሐፍ ቅዱስን በምናነብበት ጊዜ ሁሉ፣ ለሕይወት የግድ ወደ ጌታ መምጣት እና ክርስቶስ ራሱ የሆነውን የሕይወት እንጀራን መብላት አለብን—ዮሐ. 5፡39-40፤ 6፡48፣ 50-51፣ 57።
      3. ጌታን እንደ ቃሉ መብላት እርሱን እንደ የሕይወት አቅርቦታችን ወደ ውስጥ መውሰድ ነው፤ እኛ እንበላው ዘንድ እርሱ የሕይወት እንጀራ ነው—ቁ. 48፣ 51።
      4. ጌታን የመብያው መንገድ ቃሉን መጸለይ ነው፤ የእግዚአብሔርን ቃል እየጸለዩ-ማንበብ ቃሉን ለመብላት መንፈሳችንን ማንቀሳቀስ ነው—ኤፌ. 6፡17-18።
      5. የእግዚአብሔርን ቃሎች አብዝተን ስንበላ፣ አብዝተን በክርስቶስ እንቀናበራለን ፈጽመንም እንሞላለን—ገላ. 4፡19፤ ኤፌ. 3፡17፤ ቆላ. 3፡4፣ 10-11።

6. ጌታ ኢየሱስን ስንበላ ሳለን፣ ተገቢ የሆነ መንፈሳዊ የምግብ መፈጨት ሊኖረን ያስፈልገናል—ሕዝ. 2፡8—3፡3፤ ኤር. 15፡16፤ ራእ. 10፡9-10።
    ሀ. ጥሩ የሆነ የምግብ መፈጨት ካለን፣ ምግቡ ወደ ውስጡ ማንነታችን እያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ይገባ ዘንድ ክፍት መተላለፊያ መንገድ ያገኛል—ኤፌ. 3፡16-17።
    ለ. የምግብ አለመፈጨት ማለት እንደ መንፈሳዊ ምግብ ወደ የውስጥ ክፍሎቻችን ይገባ ዘንድ ለክርስቶስ ምንም መንገድ የለም ማለት ነው—ዕብ. 3፡12-13፣ 15፤ 4፡2።
    ሐ. መንፈሳዊው ምግብ በውስጣችን ክፍት መተላለፊያ መንገድ ያገኝ ዘንድ መላው ማንነታችንን ከውስጥ ክፍሎቻችን ሁሉ ጋር ለጌታ ክፍት አድርገን ማቆየት ያስፈልገናል፤ ይህንን ካደረግን፣ ተገቢ የሆነ የምግብ መፈጨት እና መዋሐድ ይኖረናል፣ እንደ መንፈሳዊ ምግብ ክርስቶስን እንመጥጠዋለን፣ ክርስቶስም ቅንብራችን ይሆናል—ቆላ. 3፡4፣ 10-11።
7. የምንበላውን ነገር ስለሆንን፣ እግዚአብሔርን እንደ ምግባችን ከበላነው፣ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ እንሆናለን እንዲሁም ተመላኪነቱን ሳይጨምር በሕይወት እና በባሕርይ እግዚአብሔርን እንሆናለን—ዮሐ. 1፡1፣ 14፤ 6፡32-33፣ 48፣ 51፣ 57።

## II. "ቃልህ ሐሤትና የልብ ደስታ ሆነኝ"—ኤር. 15፡16፡-

ሀ. ምንም እንኳን ኤርሚያስ ከሌሎች ነቢያት ሁሉ ይልቅ ቢሰቃይም፣ የእግዚአብሔርን ቃሎች ባገኘ እና በበላቸው ጊዜ ሁሉ በልቡ ሐሤት እና ደስታ ነበረው—ቁ. 16።

ለ. በቁጥር 16 *ሆነኝ* የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሐሤት እና ደስታ የጌታ ደስታ የእኛ ደስታ እንዲሆን በማድረግ፣ የእግዚአብሔር ቃሎች ወደ ውስጡ ማንነታችን ውስጥ የመበላታቸው፣ የመፈጨታቸው፣ የመዋሐዳቸው እና የመቀናበራቸው ውጤት እንደሆኑ ነው—ዮሐ. 15፡7፣ 10-11።
1. የእግዚአብሔርን ቃሎች ስንበላ፣ ቃሎቹ የልባችን ሐሤት እና ደስታ ይሆናሉ—ኤር. 15፡16።
2. የእግዚአብሔር ቃሎች ወደ ውስጣችን ከገቡ እና ወደ ውስጥ ክፍሎቻችን ዘልቀው ከተዋሐዱ በውስጥ ደስታ በውጪ ደግሞ ሐሤት ይሆናሉ።

ሐ. እግዚአብሔር የደስታ አምላክ ነው፣ እንድንደሰተውም ይፈልጋል—ነህ. 8፡10፤ መዝ. 36፡8፡-
1. በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተገለጠው ጣፋጭ ሃሳብ ድሰታችን ለመሆን እግዚአብሔር በክርስቶስ ራሱን እንደ ጸጋ ለእኛ መስጠቱ ነው—ዮሐ. 1፡14፣ 16-17፤ 2 ቆሮ. 13፡14።
2. እግዚአብሔር ከሰው ጋር ስላለው ግንኙነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባለው የመጀመሪያ ማጣቀሻ፣ እግዚአብሔር ራሱን ለሰው እንደ ምግብ አቀረበ፤ ይህ የሚያሳየን የእግዚአብሔር መሻት ድሰታችን ለመሆን ራሱን ለእኛ መስጠት እንደሆነ ነው—ዘፍ. 2፡7፣ 9፤ መዝ. 16፡11፤ ኤር. 15፡16።

መ. ሮሜ 14፡17 "በመንፈስ ቅዱስ ስለሆነ ደስታ" ይናገራል፡-
1. ይህ ጥቅስ የሚያመለክተው መንፈስ ከደስታ ጋር የተገናኘ እንደሆነ ነው፤ ደስታ የመንፈስ ባሕርይ ነው—ተዛ. 1 ተሰ. 1፡6።
2. ደስታ የመንፈስ ፍሬ ነው፤ በውስጥ የሚያድረው መንፈስ ለአማኞች ደስታን ይሰጣል—ገላ. 5፡22።
3. በመንፈስ ስንሆን፣ ደስተኞች ነን፣ ለጌታ ውዳሴዎችን እስክንዘምርና እስክንጮኽ ድረስ እጅግ ደስተኞች ነን—ተዛ. ሐዋ. 16፡25።
4. "በማይነገርና ክብር በሞላበት ሐሤት ደስ" ሊለን ይችላል—1 ጴጥ. 1፡8፡-
    ሀ. ክብር የሞላበት ሐሤት ክብር በሆነው ጌታ ውስጥ የተነከረ ሐሤት ነው፤ ስለዚህ በእግዚአብሔር መገለጥ የተሞላ ነው—ሐዋ. 7፡2፣ 55፤ 1 ጴጥ. 5፡10፤ 2 ጴጥ. 1፡3።
    ለ. በክብር ውስጥ በተነከረ ሐሤት ደስ ይለናል—1 ጴጥ. 1፡8።

## III. "የክርስቶስ ቃል በሙላት ይኑርባችሁ"—ቆላ. 3፡16 (አ.መ.ት)፡-

ሀ. የክርስቶስ ቃል በክርስቶስ የተነገረው ቃል ነው—ዮሐ. 6፡63፡-
1. በአዲስ ኪዳን ኢኮኖሚው እግዚአብሔር በልጁ ይናገራል—ዕብ. 1፡1-2።
2. ልጁ የሚናገረው በወንጌላት በራሱ ብቻ ሳይሆን በብልቶቹ፣ በሐዋርያት እና በነቢያት በኩል በሐዋርያት ሥራ፣ በመልእክቶች እና በራእይ መጽሐፍም ጭምር ነው፤ እነዚህ ሁሉ ንግግሮች የእርሱ ቃል ተደርገው መቆጠር ይችላሉ።
3. የክርስቶስ ቃል መላው አዲስ ኪዳንን ያካትታል፣ እኛም በዚህ ቃል መሞላት ያስፈልገናል—ቆላ. 3፡16።

ለ. የክርስቶስ ቃል በእውነት የክርስቶስ ማንነት ነው—ቁ. 16፤ ዮሐ. 15፡4፣ 7፡-

1. ጳውሎስ የክርስቶስን ቃል በማንነት ይመስለዋል ማለት ይቻላል፤ ቃሉ ሕያው ማንነት የሆነ ያህል በውስጣችን እንዲኖርብን ይነግረናል—ቆላ. 3፡16፤ ተዛ. ኤፌ. 3፡17።
2. በመጀመሪያ፣ ክርስቶስ እንደ ሕይወታችን አለን፤ ከዚያም በውስጣችን የሚያድረው በማንነቱ የተመሰለው ሕያው ቃሉ አለን—ቆላ. 3፡4፣ 16።
3. የክርስቶስ ቃል በውስጣችን መኖር ስለሚችል፣ ሕያው ማንነት መሆን አለበት፤ ስለዚህ የክርስቶስ ቃል በውስጣችን እንዲኖር መፍቀድ የሚያመለክተው ሕያው ማንነትን—ክርስቶስ ራሱን—በውስጣችን እንዲኖር መፍቀዳችንን ነው—ቁ. 16፤ 1፡27።

ሐ. የክርስቶስ ቃል በሙላት እንዲኖርብን እና በማንነታችን ውስጥ የመጀመሪያው ስፍራ እንዲኖረው መፍቀድ ያስፈልገናል—ቆላ. 3፡16፡-

1. *ፍቃዱ* የሚለው ቃል ትልቅ ዋጋ አለው፤ የክርስቶስ ቃል አለ፣ ነገር ግን በውስጣችን እንዲሠራ ልንፈቅድለት ያስፈልገናል።
2. የክርስቶስ ቃል በውስጣችን በሙላት መኖሩ ማለት በበለጠገ መንገድ በሁለንተናችን ይኖራል፣ በውስጣችን ያድራል ማለት ነው—ቁ. 16።
3. "ይኑርባችሁ" ተብሎ የተተረጎመው የግሪኩ ቃል በቀጥታ ሲተረጎም "በቤት ውስጥ መሆን፣" "በውስጥ ማደር፣" "በሁለንተናችን መኖር" ማለት ነው፡-
   ሀ. ይህ የሚያመለክተው የክርስቶስ ቃል በውስጣችን እንዲኖር፣ በሁለንተናችን እንዲኖር፣ ቤቱን በውስጣችን እንዲሠራ መፍቀድ እንዳለብን ነው—ቁ. 16።
   ለ. የጌታ ቃል ይሠራ እና የክርስቶስን ብልጥግናዎች ወደ ውስጣችን ያገለግል ዘንድ በውስጣችን በቂ ክፍል ሊኖረው ይገባል—ኤፌ. 3፡8።
4. የክርስቶስ ቃል በውስጣችን እንዲሠራ፣ በሁለንተናችን እንዲኖር እና በውስጣችን ቤቱን እንዲሠራ ነጻነት ሊሰጠው ይገባል—ቆላ. 3፡16።

መ. የክርስቶስን ብልጥግናዎች ወደ ማንነታችን ውስጥ በማገልገል በውስጣችን የሚሠራውን የእግዚአብሔርን ቃል አገልግሎቶች እንለማመድ ዘንድ የክርስቶስ ቃል በእኛ እንዲኖር መፍቀድ ያስፈልገናል—ኤፌ. 3፡8፡-

1. የእግዚአብሔር ቃል አብርሆት ይሰጠናል (መዝ. 119፡105፣ 130)፣ ይመግበናል (ማቴ. 4፡4፤ 1 ጢሞ. 4፡6)፣ ጥማችንንም ለመቁረጥ ያጠጣናል (ኢሳ. 55፡8-11)።
2. የእግዚአብሔር ቃል ያጠነክረናል (1 ዮሐ. 2፡14፤ ምሳ. 4፡20-22)፣ ያጥበናል (ኤፌ. 5፡26)፣ ይገነባናልም (ሐዋ. 20፡32)።
3. የእግዚአብሔር ቃል ሙሉ ያደርገናል፣ ፍጹማን ያደርገናል (2 ጢሞ. 3፡15-17)፣ እኛን በመቀደስም ያንጻናል (ዮሐ. 17፡17)።
4. የክርስቶስ ቃል በሁለንተናችን እንዲኖር በመፍቀድ እንደ የእግዚአብሔር ባሕርያት እውነታ በክርስቶስ የተሞላ አምላክ-ሰው መሆን እንችላለን—ቆላ. 3፡16-21፤ ፊልጵ. 4፡5-8።

*© 2020 Living Stream Ministry*